# የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ኅብረት (ኢዴኃኅ)
# UNITED ETHIOPIAN DEMOCRATIC FORCES (UEDF)


የካቲት 15 ቀን 1997 ዓ/ም

## ልዩ ማሳሰቢያ

ከኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ኅብረት (ኢዴኃኅ)

ለሚመለከተው ሁሉ፤

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በተለይ በዋሽንግተን ዲ.ሲ. እና እንዲሁም በአንዳንድ የሰሜን አሜሪካ ከተሞች በአገራችን በኢትዮጵያ በመጭው ግንቦት ወር 1997 ዓ/ም በሚደረገው አጠቃላይ ምርጫ የሚሳተፉ ተቃዋሚ የፖለቲካ ድርጅቶችን ለመርዳት በሚል በወገን ኢትዮጵያውያን የገንዘብ መዋጮ እንቅስቃሴ እየተደረገ መሆኑ ይታወቃል፡፡

ወገን ኢትዮጵያውያን በራሳቸው አነሳሽነት የገንዘብ መዋጮ በማድረግ በምርጫው የሚሳተፉ ድርጅቶችን ለማገዝ በመወሰናቸውና መንቀሳቀስ በመጀመራቸው የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ኅብረት ደስታውንና አድናቆቱን ይገልጻል፡፡

ይኽንን በሚመለከት ዝግጅቱን ለሚያደርገው ክፍል ስለ እንቅስቃሴአቸው ይዘትና ሒደት እንዲሁም በአንድ በኩል አዘጋጅዎቹ በሚሰጧቸው መግለጫዎች የሚደረገው መዋጮ በምርጫ ለሚሳተፉ ድርጅቶች ሁሉ መሆኑ እየተነገረ በሌላ በኩል የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ኅብረት (ኢዴኃኅ) ለምን እንዲገለል እንደተደረገ ማብራሪያ እንዲሰጠን በጥር 30 ቀን 1997 ዓ/ም በተጻፈ ግልጽ ደብዳቤ መጠየቃችን ይታወሳል፡፡

ይኽ ቅን ውጥን ሁሉን አቀፍ እንዲሆንና ቢያንስ ኅብረተሰባችንን ያላስፈላጊ በሆነ መንገድ እንዳይከፋፍልብን ያለንን ተሃስቦና አንድነታችን የሚጠነክርበትን ቀጥተኛ ሃሳብ ከአዘጋጁ ክፍል ተጠሪዎች ጋር በአካል በመገናኘት፥ ተደጋጋሚ የስልክ ውይይቶችን በማድረግና ሁኔታው በቀጥታ በሚመለከታቸውና ገለልተኛ በሆኑ አገር ወዳድ ወገኖች አማካይነት ጉዳዩ ግልጽ እንዲሆን ሞክረናል፡፡

ጥያቄአችንና የውይይቱም ይዘት አጭርና ግልጽ ነው፡፡ ይኽውም ገንዘብ ለማሰባሰብ በተቋቋመው አካል አባላት አማካይነት የሚሰነዘሩ አሳቦች የተለያዩና አንድ ወጥ ባለመሆናቸው ግልጽ ይሆንልን ዘንድ በጽሑፍ ላቀረብናቸው ጥያቄዎች በሥርዓት መልስ ይሰጠን ነው፡፡ እንደዚህ ያለ የሕዝብን ገንዘብ የሚመለከት ጉዳይ በጣም ግልጽነት፥ ተአማኒነትና ተጠሪነት ሊኖረው ያሻልና አንድም ሁሉን ያቀፈ አለበለዚያም ከሁሉም ገለልተኛ በሆነ መልኩ መካሔድ ይኖርበታል የሚል ነው፡፡

ሁሉም ድርጅቶች የቆሙበትን ዓላማ ለማሳካት የገንዘብና ልዩ ልዩ እርዳታዎችን የሚጠይቁትና የሚያገኙት ከኢትዮጵያዊ ወገናቸው መሆኑ ይታወቃል፡፡
ኅብረቱን ለመመሥረት በተደረገው እንቅስቃሴም ሆነ ኅብረቱ ከተመሠረተ ጀምሮ ለአገራችን አዲስ የሥርዓት ለውጥ ለማስገኘት በሚደረገው ሰላማዊ እንቅስቃሴና የዚህ አካል በሆነው ቀጣዩ የግንቦት 1997 ዓ/ም ምርጫ ተቃዋሚው ክፍል በተጠናከረ መልኩ በአቸናፊነት እንዲወጣ ኢዴኃኅ በሚያደርገው አገር-አቀፍ ትግል የወገን ኢትዮጵያውያን የገንዘብ፥ የሃሳብ፥ የእውቀት እርዳታ ያልተለየው በመሆኑ ኩራት ይሰማዋል፡፡


ዋና መሥሪያ ቤት (Main Office)
ፖ.ሳ.ቁ 18573 አዲስ አበባ ፤ ኢትዮጵያ
P.O.Box 18573 Addis Ababa, Ethiopia
ስልክ ቁጥር (Tel.No) 251-1530945 Ÿ (Fax)
7645

ሰሜን አሜሪካ (North America)
P.O.Box 73246
Washington DC 20056-3246, U.S.A
(Tel.No) 202-291-4217 (Fax) 202-291-

ይኸም ወገናዊ እርዳታና ትብብር በተጠናከረ መልኩ እንዲቀጥል ለዚሁ ዓላማ በበርካታ አካባቢዎች በተቋቋሙ የድጋፍ አካሎች አማካይነት ያልተቋረጠ እንቅስቃሴዎችን በማድረግ ላይ ነው።

አሥራ አራት አባላትን ያቀፈውና ከአንድ ዓመት ከሰባት ወራት በላይ ኅልውና ያለው የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ኅብረት በምርጫው ሂደት መሳተፉ ግልጽ ሆኖ እያለ ለምን ስለጉዳዩ እንዲያውቅ እንዳልተደረገም ሆነ ስለ ግብረ-ኃይሉ አሠራር እስካሁን መልስ እንዳልተሰጠን ፈጽሞ ግልጽ ሊሆንልን አልቻለም።

በኛ በኩል ይኸንን ጥረትና እንቅስቃሴ የጋራ እንድናደርገውና ለአንድ ተመሳሳይ ዓላማ ወገኖችንን በተናጠልና ለየብቻ እየቀረብን እንዳናስቸግረው፤ ቢያንስ ግን የሚሰበሰበው የሕዝብ ገንዘብ ለሁሉም ሳይሆን ለተወሰኑ ድርጅቶች ብቻ መሆኑን በማያሻማ መንገድ ለባለጉዳዩ ሕዝብ ግልጽ እንዲደረግ በተደጋጋሚ ተማጥነን አድማጭ አላገኘንም።

ኅብረቱ እንኳን በተቃዋሚው ጎራ ለተሰለፈ ኃይል ለማንም ወገን የሚደረግ እርዳታን ከልብ ይደግፋል፥ ያበረታታልም። ለሚያዋጣው ወገኖችን ግን እርዳታው ለማን እንደሆነ በማያሻማና በነጠረ መልኩ ግልጽ ሊደረግለት ይገባል።
ይኸንን ለሕዝብ በግልጽ ማሳወቅ ለምን እንዳልተፈለገና ሁሉም ሳይኖሩበት በደፈናው ለሁሉም ነው ብሎ ገንዘብ ከሕዝብ ለመሰብሰብ መሞከር አግባብነት የሌለውና ሕገወጥ መሆኑንም በሃዘኔታ መግለጽ እንወዳለን።

ስለሆነም፤

1. ሁሉን አቀፍ እንዲሆን ብዙ ጥረት ብናደርግም በዚህ ግብረ-ኃይል አማካይነት በሚደረግ የገንዘብ መዋጮ እንቅስቃሴ ውስጥ ኅብረቱን ለመጨመር አለመፈለጉን ስለተረዳንና በመሆኑም ከዚህ መዋጮ ኅብረቱም ሆነ አንድም የኅብረቱ አባል ድርጅት ተጠቃሚ ወይም ተካፋይ ባለመሆኑ፥
2. ኅብረቱ ለሚያደርገው አገር-አቀፍ ትግል አሁንም የኢትዮጵያዊ ወገኑን እርዳታ እንደሚጠይቅ፥
   በትህትናና በአክብሮት ይገልጻል።

የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ኅብረት ለሚያደርገው አገር-አቀፍ ትግል ማገዣ በቅርቡ በምናደጋቸው የእርዳታ ማሰባሰቢያ ዝግጅቶች እየተገኛችሁ እርዳታችሁን እንድትለግሱን ወገናዊ ጥሪያችንን በአክብሮት ስናቀርብ ኅብረቱ ሕጋዊ ሆኖ የሚንቀሳቀስ በመሆኑ በሚቀጥለው የባንክ ሂስብ የምትችሉትን የገንዘብ እርዳታ እንድትልኩልን ስንጠይቅ ከወዲሁ ወገናዊ ምስጋናችንን በማቅረብ ነው።

Chevy Chase Bank,
Account # 0044378793
Routing # 255071981

ኅብረት ለድል!!
ድል በኅብረት!!!
ኢትዮጵያ በልጆቿ ኅብረት ታፍራና ተከብራ ትኖራለች!!!!

የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ኅብረት